ፀጋዬ



ደብተራው

# ኢትዮጵያ


መስከረም 2005

በነጻ የሚሰራጭ



የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት የአውሮፓ ክፍል ተመሰረተ

ገጽ 4

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ደብዳቤ ጻፈ

ገጽ 3

የቀዩ ሽብር ወንጀለኛ ተያዘ

ገጽ 3


## ያስለቃሽ አልቃሾች

ተጠቃሚና አድርባይ በወያኔ ኤምባሲ ውስጥ፣ በመለስ ትእዛዝ ለተጨፈጨፉት ተቆርቋሪዎች ከወያኔ ኤምባሲ ውጭ ተፋጠው ዋሉ።


ገጽ 3








## ኢሕአፓ 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን በተሳካ ሁናቴ አጠናቀቀ

40 ክረምትና 40 በጋ ትግል የተፈረረቀበት ኢሕአፓ የውስጡንና የውጪውን አሜኬላ ተቋቁሞ ጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ያሴሩበትን ሴራ አቸንፎ ህልውናውን በመጠበቅ እነሆ ባለፈው ከነሐሴ 22-ነሕሴ 26 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ከዓለም ዙሪያ በተወከሉ ተሰብሳቢዎች አማካይነት አጠናቋል። ይህንኑ አስመልክቶ ድርጅቱ ያወጣውን መግለጫ በገጽ 3 ይመልከቱት።

## ኢሕአፓ 40ኛ አመት የምሥረታ በዓሉን በደመቀ ሁኔታ አከበረ

## " በቆራጥ ልጆቿ ኢትዮጵያ ከወደቀችበት ትነሳለች"

### ዶ/ር ዘነበ


ኢሕአፓ 40ኛው ዓመት የምሥረታ በዓሉን ነሐሴ 26 2004 እዚህ ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ እጅግ ደማቅ በሆነ ሁኔታ አከበረ፡፡

ቅዳሜ ዕለት ከረፋዱ 5 ሰዓት ጀምሮ እስከ እኩለ ለሊት በዘለቀው በዚህ የልደት በዓል ላይ የድርጅቱ ደጋፊዎች፣ ከተለያዩ ዓለማት የተሰባሰቡ አባላት፣ ከፍተኛ አመራሮች እና ተጋባዥ እንግዶች የተገኙ ሲሆን በእለቱ በአዳራሹ ውስጥ በርካታ ታዳሚዎች መገኘታቸውን በስፍራው ተገኝተን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ዝግጅቱ ከተጠበቀው በላይ እጅግ አስደሳች ከመሆኑም በተጨማሪ በአዳራሹ የተገኙት ህጻናት፣አረጋውያን እና ወጣቶች በሙሉ ስሜታችው ተሳታፊ እንደነበሩም ታዝበናል፡፡ በሀገራችን ፍትህ፣እኩልነት እና ዴሞክራሲ ለማምጣት ሲሉ ህይወታቸውን ላጡ የኢሕአፓ አባላት የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት በማድረስ የተጀመረውን የዝግጅቱን ሥነ-ስርዓት ተከትሎ የመክፈቻ ንግግር፣ መዝሙሮች፣ ግጥሞች፣ የጨረታ ሥነ ስርአት፣አዝናኝ የባህል ሙዚቃዎች እና ሌሎች መርሓግብሮች እንደቅደም ተከተላቸው ሰዓታቸውን ጠብቀው ቀርበዋል፡፡

አጭር የመክፈቻ ንግግር ካደረገ በሁላ ለሰማዕታቱ የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት እንዲደረግ የጠየቀው ተወዳጁ ገጣሚ አሊ ሁሴን፣ የድርጅቱን ከፍተኛ አመራር ዶ/ር ዘነበ፣ 40ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን አስመልክተው ንግግር እንዲያደርጉ በመጋበዝ ሥነ-ስርዓቱ ተጀምሯል፡፡ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የሆኑት ዶ/ር ዘነበ፣ የኢህአፓን 40ኛ ዓመት የምስረታ በዓልን አስመልክተው አባላቱን ፣ደጋፊዎቹን እንዲሁም በትግል የተሰውትን ጓዶች የቅርብ ዘመዶቻቸውን እንኳን ለዚህች ቀን በሰላም አደረሳችሁ፤ በትግሉ ወቅት የተሰውትን ደግሞ አፈር ይቅለላቸው ካሉ በኋላ፣ከመስራቹ አንዱ የሆኑትን እና አሁንም በጽናት እየታገሉ ያሉትን አቶ እያሱ አለማየሁን እንኳን ለ40ኛ ዓመት የምስረታ በዓል በሰላም አደረሰዎት በማለት ጀምረው ወቅታዊና ቀደም ባሉ ጉዳዮች ላይ ዳሰሳ በማድረግ አጠር ያለ ንግግር አድርገዋል፡፡ ዶ/ር ዘነበ በንግግራቸው፣ ኢሕአፓ ጠላት ያደረሰበት ጥቃት ሳያስበረግገው ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ነገሮችን እያገናዘበ በጽናት የሚታገል መሆኑን፤ የአዬውን እና የደርግን ሥርዓት ለማስወገድ አስተዋጽኦ ማድረጉን፤ ኢሕአፓ የደረሰበትን ጥቃት ተቋቁሞ እዚህ መድረሱ የሚደነቅና ለሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ትምህርት ሊሆን እንደሚችል፤ ኢሕአፓ በትግሉ መራዘም ምክንያት ለሥልጣን አለሙብቃቱ ሽንፈት የሚመስላችው መሳሳታቸውን፤ ፀረ-ሕዝብ የሆኑ ወገኖች፣ መስካሪ የሌለ እየመሰላቸው የኢሕአፓን ታሪክ ሊያበላሹ ቢሞክሩ እንደማይቻላቸው፤ ድርጅቱ ቀደም ሲል የገባውን ቃል ኪዳን አሁንም በካህዲዎች ሳይሸነፍ መቀጠሉን፤የወያኔን አገዛዝ ታግሎ ማሸነፍ የኢሕአፓ አቋም መሆኑን፤ ኢሕአፓ አስፈጀን አሁንም ሊያስፈጀን ነው ለሚሉ ጆሮ እንደማይሰጣቸው፤ ኢሕአፓ የህብረት ጥሪ ቢያቀርብም ተገቢ የሆነ ምላሽአለማግኘቱን… በማተት በመጨረሻም "ኢትዮጵያ በቆራጥ ጀግኖች ልጆቿ ከወደቀችበት ትነሳለች" በማለት ንግግራቸውን ቋጭተዋል፡፡ከዶ/ር ንግግር በመቀጠል ገጣሚ አሊ ሁሴን መድረኩን በማያዝ ጣፋጭ የሆኑ ግጥሞቹን ለታዳሚው አስደምጧል፡፡ ገጣሚ አሊ ለታዳሚው በደረቁ


ወደ ገጽ 3 ዞሮእል








ኢትዮጵያ
በኢሕአፓ የዲሲ ሪጅን ደጋፊ ኮሚቴ
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ
አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd fl. Washington DC 20011
ስ/ቁ 202 291 4217 ኢሜል dc.region.eprp@gmail.com

## ርዕሰ አንቀጽ

**"ጠላትህን ዉሃ ሲወስደዉ ብታይ ምራቅህን አክልበት፤''**

አምባገነኑ የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ከሰሞኑ ሞቶ መቀበሩ ተነግሯል ። በሰንደቅ ዓላማችን ክብር በተዛበተበትጊዜ ፤ የብሔራዊ ታሪካችንን ዕድሜ ከአንድ ምዕተ ዓመት በታች አሳንሶ በተሳለቀበት ወቅት በብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን ልቡና ዉስጥ ከሙት ተቆጥሯልና አካላዊ ሞቱና ቀብሩ አዲስ ዜና አልሆነም ። ከዚህ አንጻር ፤ ሞቱ በብሔራዊ ደረጃ ከተበሰረበት ጊዜ አንስቶ ዕኩያኑ ወያኔዎችና ሆዳም ተከታዮቻቸዉ ተሰናባቹ መሪያቸዉ ያልፈጠረበትን ሕዝባዊነት ሊያላብሱት በመገናኛ ብዙሐን አማካይነት የከረሙበት መናኛ ዘመቻና ያቀረቧቸዉ ቧልታይ ትዕይንቶች የገዛ ራሳቸዉን ያጃጅሉባቸዉ እንደሁ እንጂ ቀልብ ለመሳብ የሚያበቋቸዉ አይደሉም። በሕይወቱ ሳለ ኢትዮጵያዊነት እንደ ከፋ ህልም ሲያስደነብረዉ የኖረዉን አሳፋሪ ሰብዕናዉን ካስተዋለ ሕዝብ ፊት የሬሳ ሣጥኑን በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጠቅልሎ በሰልፍ መንጎማለልም እንደዚሁነዉ፤ትርጉም የለሽና ትዝብትን የማይፈሩ ጀብደኞች ብቻ የሚዳፈሩት ወራዳ ተግባር ። ሰዉዬዉ ቢያዉቅበት ፤ በታሪክ አጋጣሚ ፤ ከህያዋኑ ታላላቅ ኢትዮጵያዉያን መሃከል ለመቆጠር የሚያበቃ ሥራ ሊሠራ ከሚችልበት ልዩ ደረጃ ላይ የመቀመጥ ዕድል ገጥሞት ነበር ። በፈላጭ ቆራጭነት ከተንጠለጠለበት የሥልጣን ማማ ላይ በቆዬበት የሃያ አንድ ዓመት ከ፲፩ ሳምንታት ጊዜ የሌሎችን ብቻ ሳይሆን የራሱንም የሥራ ድርሻ እንዳሻዉ በመፐወዝ፤ምጻጉዕ አስተሳሰቡንና ትንሽ ሰዉነቱን ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር በተሰኙ ማዕረጎች ሲያሞካሽና ሲቀማጠል ቆይቷል ። ሃያ አንድ ዓመታት ድህነትና በሽታ ተነባብረዉ ከሚያጠቁት ከብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ማዕከላዊ ዕድሜ አንጻር ሲለኩ እጅግ በጣም ረዥም ዘመናት ናቸዉ ።በዓለም ደረጃም ቢሆን የአንድ ትዉልድ የቆይታ ዘመን ተደርጎ ከሚታመንበት አማካይ ዕድሜ ጋር ብዙ አይተናነስም ።በዚህ የጊዜ ርዝማኔ ዉስጥ ለአገሩ ክብርና ለነጻነቱ ቀናዒ ለሆነዉ ሕዝብ በአመዛኙአንገትየሚያስደፋ ብሔራዊ ዉርደት ነዉ የተረፈዉ።

ኢትዮጵያና ሕዝቧ ለአያሌ ዘመናት በጦርና በዲፕሎማስያዊ ትግል አስከብረዉ ያቆዩትን የባህር በር ባለቤትነት የተነጠቁት በዘመነ መለስ ነዉ ። አገሪቱ በጎሳ የተሸነሸነችዉም ሆነ ዐይን ያወጣ የዘር መድልዎና ሙስና የነገሰባት ይኼዉ ሰዉና የወንጀል ተባባሪዎቹ በፈላጭ ቆራጭነት ቀይሰዉ በመሠረቱት ስርዓት ዉስጥ ነዉ ። ዛሬ በሞቱ በተገላገለችዉ አገር ዉስጥ በቀን ሦስት ጊዜ መመገብ ከቅንጦት ይቆጠራል ። ዜጎች በገፍ ይሰደዳሉ ፤ ይሳደዱማል ። አያሌዎች በጠራራ ጸሀይ ተገድለዋል ፤ በርካታዎችም ደብዛቸዉ ጠፍቷል ።የሀገሪቱን የፍትህ ፤ የትምህርት ፤የገንዘብ ፤...ወዘተ ተቋማት በየተራ በመንቀስ ያለባቸዉን ልምሾ ለሥርዓቱ ሰንካላነት ማጠየቅያ ማቅረብ ይቻላል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ መሰሉ ጽልመታዊ የወያኔ ሥርዓት ሞትና ቀብር አምርሮ ይታገላል ፤ እንጂ ለቀንደኛዉ አምባገነን ህልፈት ከልቡ አያነባም ። በቁሙ ሳለ በፈጸማቸዉ ዕኩይ ተግባራት ትዉስታ በሙብገን በሥርዓቱ ላይ ያምጻል ፤ እንጂ በአደባባይ ቆሞ ደረቱን አይደቃም ። ለዘረኛዉ አገዛዝ ቁንጮ የነበረዉ ሰዉዬ ሞት በራሱ ለዴሞክራሲያዊዉ ሥርዓት ምጽአት በምር ለሚታገሉት ኃይሎች የመጨረሻ ግብ አይደለም ። ቢሆንም ድንገቱ ከአጠቃላዩ ወያኔያዊ የአገዛዝ ዉቅር ላይ የበኩሉን ስንጥቅ ወይም ንቃቃት ጥሎ ማለፉም አይቀሬ ነዉ።ስንጥቁ ቀስ በቀስ የአገዛዙ ምርጦችና ስዬመ ጎሳ ደናቁርት ወደሚንደላቀቁባት የወያኔ መርከብ ዉሃ ማስገባቱ የግድ ይሆናል። በዚሁ ዞግ ከሚፈጠረዉ የዉሃ ሙላትና ተቀጣጣይ እሳት ለመዳን ቀድመዉ ለመዝለል የሚሽቀዳደሙት ደግሞ የደለቡቱ የሥርዓቱ አይጦች መሆናቸዉ አይጠረጠርም ። በመሆኑም ይህ ስንጥቅ እንዳይጠገን በክፍተቱ ዉሻል በማስገባት ሥርዓቱ ከነአካቴዉ የሚደረመስበትን መላ የመምታቱ ጉዳይ በሕዝቡ መሀከል ሆነዉ ተጨባጭ ትግል በማድረግ ላይ ለሚገኙቱ ሀቀኛ የአንድነትና ዴሞክራስያዊ ኃይሎች የሚተዉ ፤ይዋል ይደር የማይባል ጉዳይ ነዉ ። ወያኔና እበላ ባይ ተከታዮቹ በአለቃቸዉ ሞት ሳቢያ የተቆረጠ ራሳቸዉን መልሰዉ ለማብቀል የሚሹትን ጊዜ ለመግዛት በኃይለ ማርያምም ሆነ በወልደማርያም ስም ለሚያሰሙት የ "ተለዉጫለሁ" ተማጽኖና የድርድር ጥሪ ተበልጦ ትጥቅን አለመፍታት ሥርዓቱን ከሚታገሉት ወገኖች ሁሉ ይጠበቃል።የዚያኑ ያህል ፤በተረትና ምሳሌ እንደምናዉቀዉ አሞራ ፤ሕዝባዊዉን ትግል ቅል አድርገዉ በአፋቸዉ በማንጠልጠል ወደ ወያኔዎቹ ሰፈር ለሙብረር የሚቋምጡትን "አርበኞች" እግር በእግር እየተከታተሉ አፍራሽ ማንነታቸዉን ማጋለጥ ይጠበቅባቸዋል ። የምንወዳትን ሀገር፤ ከሰማንያ ሚልዮን በላይ የሚቆጠር ሕዝቧንና የተከታዮቹን ትዉልዶች ዕጣ በሚመለከት ቀልዱ መቆም አለበት ።

ዴሞክራስያዊዉ ሕዝባዊ ትግል ያቸንፋል /

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በነጻነት ኮርታ ትኑር /

# ደብዳቤዎች

## ገመና ድራማ ቁጥር 3

የነፍሰ ገዳዩ የመለስ ዜናዊ ሞት እንደተሰማ፣ ባገር ቤት ያለው ሕዝብ ምንም እንኳን ደስታውን ባደባባይ መግለጽ ባይችልም፣ በብሔር የከፋፈለው፣ኤርትራን ያስገነጠለ፣ አዕላፍ ኢትዮጵያውያንን የጨፈጨፈ....ወዘተ መለስ ዜናዊ መሞቱን ሲሰማ ውስጥ ውስጡን ደስ እንደሚለው ጥርጥር የለውም:: እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ግን በተገላቢጦሽ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመለስ ዜናዊ ሞት አዝኖ እምባ ተራጨ፣ የሳቸውን ራዕይ ይዘን እንቀጥላለን አለ የሚለውን የወያኔን አሰልቺ ድራማ ስሰማ በበኩሌ የሌባ አይነ ደረቅ...ነው ያልኩት:: እንደኔው ሁኔታውን በጥሞና የታዘቡት የዘመኑ ወጣቶች ግን ሁኔታውን በጥሩ አገላለጽ አቅርበውታል፡ ገመና ድራማ ቁጥር 3 በሚል-ድንቅ አገላለጽ::

ታማኙ ከዋሽንግተን

## አይ ኢትዮጵያ!

ወይዘሮ አዜብ ጎላ በመለስ ሬሳ ሽኝት ወቅት በመስቀል አደባባይ ለተሰበሰበው ህዝብና ዲፕሎማቶች ንግግር አድርጋ ነበር::አዜብ በዚህ ንግግሯ የመለስ ራዕዮችን፣ ስትራቴጂ ዎችን እና ፖሊሲዮችን እስካልተበረዙ ድረስ እኔም የሱን ስትራቴጂ እና ፓሊሲ ለማስቀ ጠል የበኩሌን አስተዋጽኦ አደርጋለሁ ማለቷን አስታውሳለሁ::ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም ይባላል:: አረ ለመሆኑ ወ/ሮ አዜብ ስትራቴጂ ወይም ፖሊሲ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለች ወይ?! እሱስ ይሁን ለመሆኑ ስትራቴጂዎቹን እና ፖሊሲ ዎቹን አስረጂ ብትባል በምን ቋንቋ ልታስረዳ ነው? ባማርኛ እንዳንል እንደሰማናት ከሆነ አማርኛ አትችልም፤ በእንግሊዘኛ እንዳንል በስተርጅና ሲቨል ሰርቪስ ኮሌጅ ተምራ ስትራቴጂ ምን እንደሆነ ለመግለጽ የሚያስችል እንግሊዘኛ ትችላለች ተብሎ አይታሰብም:: እርግጥ ነው የመለስ ፖሊሲ መግደል እና መዝረፍ...ወዘተ ስለሆነ መማር አያስፈልገውም ብላ ከሆነ በሱ እስማማለሁ...አይ ኢትዮጵያ!

ደሰታ ከዋሽንግተን

## የባሰ አታምጣ

ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ እንደተመረጠ ሰሞን አንድ የተናገረውን ወይም የጻፈውን ነገር አስታውሳለሁ:: ፕሬዚዳንቱ በዚህ ጽሁፉ ወይም ንግግሩ፣ የአፍሪካ አምባገነኖችን በተመለከተ እንዲህ ብሎ ነበር:: ከዚህ በፊት በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት እንደ ሞቡቱ ሴሴሴኮ አይነት አምባገነኖችን ስንረዳ የነበረው በሁለት ዓለም ጎራ ምክንያት ነው:: አሁን ግን አንደኛው ጎራ ኮሚኒዝም ስለፈረሰ ለአምባገነኖች ቦታ የለንም ብሎ ነበር:: ይሁን እና በቀደም ዕለት ሱዛን ራይስ ለመለስ ዜናዊ ያደረገችውን ሙገሳና ወዳሴ ስሰማ በጣም ነው ያፈርኩት:: ከዚህ የምንረዳው ምዕራባውያን ለጥቅማቸው ሲሉ የት ድረስ ሊሄዱ እነደሚችሉ ነው:: ትልቁ አደጋ ያለው እዚህ ላይ ይመስለኛል:: የባሰ አታምጣ እንጂ ሌላ ምን ይባላል::

እውነቱ ከሜሪላንድ

## ይድረስ ለ"ኢትዮጵያ" አዘጋጆች

በቅድሚያ በጀመራችሁት ታላቅ ሥራ ቀጥሉ እላለሁ። በመጨረሻ እትማችሁ ስለጸጋዬ ደብተራው ያቀረባችሁት ድንቅ ሆኖ ሳለ የጸጋዬ ቅኔዎች ግን በዓመታዊው የኮሌጁ የግጥም ውድድር ወቅት የቀረቡ ሳይሆኑ በኮሌጁ የተማሪ ማህበር መጽሔት ላይ የወጡ ነበሩ። ለዓመታዊው ውድድር ያቀረበው "ኖስትምስለኪ" የሚለውን ይመስለኛል።

በርቱ

ይትባረክ ደምጸ

****

ለስጡን አስተያየት እናመሰግናለን።"ማን ይመስክር ያይ .. ማን ይናገር የነበረ።"

ከኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች

## ውድ ከዳ

ከኢትዮጵያ የላኩልን ጽሁፎች ደርሰውናል። የመጀመርያ ጽሁፍዎ በዚህ እትም በነጻ ዓምድ ሥር ይነበባል። ስምዎን በምጻረ ቃል ያሠፈርነው የሰጡን ስም የብእር ስም ስለመሆኑ እርግጠኛ ባለመሆናችን ነው።

ከ"ኢትዮጵያ" ጋዜጣ አዘጋጆች

ከገጽ 1 የዞረ

## ኢሕአፓ 40ኛ አመት የምስረታ በአሉን በደመቀ ሁኔታ አከበረ

ግጥሞቹን አንብቦ የሚወርድ ሳይሆን ዘና በሚያደርግ ንግግሩ ጭምር ተመልካቹን የሚያዝናና ታላቅ የመድረክ ሰው ነው፡፡ እንደ ገጣሚ አሊ ሁሉ ግጥሞቹን ለታዳሚው ያስደመጠው ሌላኛው ገጣሚ እና ጋአዜጠኛ ፃዲቅ ነበር፡፡በወቅቱ ወጣቶቹ የሙዚቃ ተጫዋቾች ለታዳሚው ያቀረቡት ባህላዊ ጫዋታ እጅግ አስደሳች ከመሆኑ የተነሳ በጣም በርካታ ተመልካቾች ወደ መድረኩ በመውጣት እስክስታውን መቀላቀላቸው ግድ ነበር፡፡

አንጋፋዋ የመድረክ ሰውና አቀንቃኟ ጠለላ ከበደ ደግሞ ሰው ከተሰማራ የሚለውን የብዙነሽ ዘፈንን በማቅረብ፣ ተምሳሌቱን የኢሕአፓ አንጋፋ ታጋዮች አዲስ ወጣት ታጋዮችን ማፍራታቸውን፣ እነሱም ዳግመኛ ሊያገሡ መዘጋጀታቸውን የሚገልጽ መልዕክት ያዘለውን ዘፈኗን በተስረቅራቂ ድምጿ ስታዜም ከተመልካቹ ያድናቆት ጭብጨባ ተቸሯታል፡፡ እሷን ተከትለው ደግሞ የኢወክንድ ወጣቶች ያደራ ቃል አለብኝ የሚለውን መዝሙር በመዘመር ለበአሉ ታላቅ ድምቀት ሰጥተውታል፡፡ ሌላው ለበአሉ ደምቀት የሰጠው ነገር ቢኖር ለጨረታ የቀረበው ክራርን ለማሸነፍ የተደረገው ፉክክር ነበር፡፡ገጣሚ አሊ ሁሴን በ 20 ዶላር ያስጀመረው ጨረታ ከሁለት ሺ ዶላር በላይ በሆነ ዋጋ ተጠናቋል፡፡ይህውም ክራሩ ከተገመተው የጨረታ ዋጋ በላይ ነበር፡፡ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ አባላቱ እና ደጋፊዎቹድርጅቱን በገንዘብ ለመርዳት ያላቸውን ተነሳሽነት የሚያሳይ ነው ተብሏል፡፡በመጨረሻም፣ **የትግሉ ነው ሕይወቱ** የሚለው መዝሙር ተዘምሮ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል፡፡

የትግሉ ነው ሕይወቱ...

ልጓዝ በድል ጎዳና

በተሰውት ጓዶች ፋና...

እያሉ አባላቱና ደጋፊዎቹ ሲዘምሩ ስሜታቸው እጅግ ከፍተኛ ነበር፡፡

## ያስለቃሽ አልቃሾች

ኢትዮጵያን በቅጥረኝነት ተሰልፎ በዘረኝነት ተንሰፍስፎ የጎዳት ሥራአት ቁንጮ መለስ ዜናዊ ድንገት ያለፍርድ እንደሰው ስለሞተ የሥርዓቱ አጫፋሪዎች ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የወያኔ ጽ/ቤት ሊይደርጉት በነበረው የለቅሶ ውሎ አገራችንን ላጠፋ መለስ አይለቀስ በማለት ነበር ኢትዮጵያዊው ዳግም ጨዋነቱን በተቃውሞ ያስመሰከረው። በሺ የሚቆጠሩ የመለስ ዜናዊ ሰለባ የሆኑ ወገኖችን ፎቶና ስም ዝርዝር የያዙ ሰልፈኞች ለአምስት ሰዓታት በሽለላና በፉከራ ኢትዮጵያዊ ወኔና ጨዋነትን ሲያንጸባርቁ በወዲያ ማዶ የተሰለፉ የወያኔ ጉጅሌዎች በጥቁር ጨርቅ ተጠቅልለው የመሀል ጣታቸውን ትንሿም አረጋዊቷም ሲያስመርቁ በዓለም ዙርያ በዩትዩብ እና በኢትዩብ ለእይታ በቅተዋል። ለሥርዓቱ ሞት፣ ለወያኔ ሞት እያሉ እየፎከሩ አለ ገና አለ ገና የበረከት አለ ገና የስባትም አለ ገና አለ ገናን እየዘመሩ በዋሽንግተን ፖሊሶች ገላጋይነት በዚህ አገር አቆጣጠር ከእኩለ ቀን ጀምረው በአምስት ሰዓት ከሰአት በኋላ አጠናቀዋል።

በወቅቱ ከወያኔ ጉጅሌዎች ይሰሙ የነበሩ ኢትዮጵያን የሚሳደቡ ጢያፍ ቃላቶችን እዚህ ላይ አይደገምም እንጂ ቢደገም ኖሮ ወያኔ ትላንትም ወያኔ ዛሬም ወያኔ ነገም ወያኔ መሆኑን አመላካች ነበር በማለት ብዙዎች ይስማሙበታል።

የኢትዮያ ጋዜጣ ዘጋቢ እንደዘገበው።

## የቀዩ ሽብር ወንጀለኛ ተያዘ

በቀይ ሽብር ዘመን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በእስረኞች ላይ ሰቆቃና ግድያ በመፈጸም የተጠረጠረዉ፤ ከፈለኝ ወርቁ የተባለ ግለሰብ ዴንቨር/ኮሎራዶ ዉስጥ ተይዞ ክስ እንደተመሰረተበት ሳምንታዊዉ ዘ ዴንቨር ፖስት ጋዜጣ ዘገበ፡፡ተከሳሹን ለፖሊስ ጠቁሞ ያስያዘውና ማንነቱ እንዳይገለጽ፤ ኬ.ኬ(k.k) በሚል የሙሉ ስሙ መጀመሪያ ፊደላት መጠራትን የሚመርጠዉ ሰው በቀይ ሽብር ወቅት ከፍተኛ 15 ዉስጥ ታስሮ የነበረና፣ ከፈለኝ አለሙ በእስረኞች ላይ ሰቆቃ ሲፈጽም የተመለከተ ሰው ነው፡፡

ኬ፣ኬ(k.k) አንድ ቀን በግንቦት ወር ዴንቨር፣ አውሮራ፣ ሀቫና ጎዳና ላይ በሚገኘው ሬስቶራንት ውስጥ በመስተናገድ ላይ ሳለ ነበር ከ30 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የእስር ቤት ሹም የነበረውን ከፈለኝ አለሙን የተመለከተው። እንደ አሜሪካዊው የጸጥታ ክፍል ሀላፊ ጄፈሪ ሊምቡክ ምስክርነት ከሆነ፣ ማክሰኞ በ 09/05/12 በዋለው ችሎት የተገኘዉ ኬ.ኬ ፤ከፈለኝ አለሙ ወርቁን፣ "አንተ ከፈለኝ አለሙ ወርቁ አይደለህምን?" በሚል ጥያቄ አፋጥጦታል፡፡ተከሳሹ በዴንቨር የፓርኪንግ ሰራተኛ መሆኑ ሲታወቅ ክሱ የተመሠረተበት ከፈለኝ አለሙ በሚለዉ መጠሪያዉ ሳይሆን፣ ጆን ዶ (Jhon Doe) በሚለዉና በአሠሪዉ ዘንድ በሚታወቅበት ስሙ ነዉ ። እንደ ዴንቨር ፌደራል ግዛት ሀላፊዎች ከሆነ ጆን ዶ በሚል ስም የሚታወቀው ይህ ሰው በርግጥም ሀብተአብ ተማኑ በሚል ሌላ ስም የሚታወቅና በኢትጵያ ከፍተኛ 15 ውስጥ የእስር ቤት ሹም እንደነበር ተረጋግጧል ። ከፈለኝ አለሙ ወርቁ ኢትዮጵያ ወስጥ በፈጸመው ወንጀል አልተከሰሰም። በዚህ ፈንታ የፌደራሉ ባለስልጣናት ክስ የመሰረቱበት ለኢሚግሬሽን ያቀረበዉን መረጃና የማስረጃ ሰነዶች በተመለከተ በመዋሸቱ፣ በማንነት ስርቆሽ እና የስደተኛ ህጉን ጥሶ በመገኘቱ ነው፡፡

የደህንነት ባለስልጣኑ እንደገለጸው ከሆነ ከፈለኝ አለሙ ወርቁ በ 2004 ወደ አሜሪካ ከመምጣቱ በፊት ኬኒያ ውስጥ ለ 13 ዓመታት ኖሯል፡፡ በተጨማሪም ኬኒያ ወስጥ አንድ ልጅ እንዳለውና አሁንም ድረስ ለልጁ ገንዘብ እንደሚልክ፣ ወንድሙ ደግሞ በኢትዮጵያ ወስጥ የሆስፒታል ባለቤት እንደሆነ ጄፈሪ ጨምሮ ገልጿል፡፡ማክሰኞ ዕለት በዋለው ችሎት የከፈለኝ አለሙ ጠበቃ ተከሳሹን በተደጋጋሚ ጆን ዶ እያለ ሲጠራው ተደምጧል፡፡ከፈለኝ አለሙ ሴንትራል ፓርኪንግ ወስጥ በሰአት 10 ዶላር እየተከፈለው የሚሰራ ሲሆን፣ በ 2010 ዓ.ም የአሜሪካ ዜግነት ማግኘቱንም ጠበቃው ጨምሮ ገልጿል።

ከከፈለኝ አለሙ ወርቁ መኖሪያ ቤት በከፊል የተሞላ ማመልከቻ ከመገኘቱ በስተቀር ፓስፖርት እንደሌለው የደህንነቱ ሰው ጄፈሪ ተናግሯል፡፡ማክሰኞ ዕለት በዋለው ችሎት የከፈለኝ ወርቁ ጠበቃ፣ ደንበኛው ካገር ይወጣል ተብሎ የሚያሰጋና የትም መሄጃ ስለሌለው በዋስ እንዲለቀቅ ፍርድ ቤቱን ጠይቋል፡፡ "ይህ ግለሰብ በአሜሪካ ውስጥ ማንንም ሰው መጉዳቱን የሚያመለክት ታሪክ የለውም" ሲል ጠበቃው ጨምሮ ተከራክሯል፡፡ከሳሹ አቃቤ ህግ ደግሞ በበኩሉ ፤ ተከሳሹ በአሜሪካ ውስጥ ተይዞ ባያውቅም፤ የወንጀል ታሪክ ባይኖረውም፣ እንዲለቀቅ መፈቀድ የለበትም ሲል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራሉ ሪኮርድ እንደሚያመለክተው ተከሳሹ ቢያንስ ሦስት ተለዋጭ ስሞች እንዳሉት ያሳያል ሲል ፍርድ ቤቱ አመልክቷል፡፡ በመጨረሻም ፍርድቤቱ ከፈለኝ አለሙ ወርቁ በቀጠሮዉ ዕለት ፍ/ቤት እስኪቀርብ ድረስ ታስሮ እንዲቆይ ወስኗል።

ከገጽ 6 የዞረ

## <<እየሞተ>> ያለዉ የምሑራን የፖለቲካ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ፤ ድሮና ዘንድሮ

የሚማቅቀዉን ህዝባቸዉን መታደግ መሆኑን ተገንዝበዉ ነዉ ባይ ነኝ፡፡ ምናልባትም ዝምጭጬ የ ሎሌነት መገለጫ ነዉ አሊያም ህዝባዊ ሀላፊነትን ከመዘንጋት ነዉ ቢባል ሳይሻል አይቀርም ፡፡ እርግጥ ነዉ <<የዝምጭጬን>> ጉዳይ አስቀድሜ አነሳሁት እንጅ ከዛም ባለፈ ለጥቅማጥቅምና ስልጣን ሲሉ ተቸግሮ ያስተማራቸዉ.ንና ከነሱ ብዙ የሚጠብቀዉን ደሀ ህዝብ ወደጎን ገፍትሮ ከአምባገነኖች ጎን መቆምና ለነሱ ክብርና ስልጣን እንዲሁም ረጅም እድሜ <<የወዳሴ>> ቃላትን መደርደርም በምሑራን አካባቢ እየተለመደ መጥቷል፡፡ በርግጥም በማህበረሰባችን ላይ ጭቆናን የጫነዉ አገዛዝ ተማረ በሚባለዉ የህብረተሰብ ክፍል የተገነባና የተደገፈ ነዉ ፡፡ እናም ባጠቃላይ የዛሬዎቹን ምሑራን ከትናንትነዎቹ ጋር ሳነፃፅራቸዉ ብዙ የዘነጉት ነገር እንዳለ ይታየኛል፡፡ ከነሱ በማይጠበቅ ሁኔታ በህዝብ ላይ ግፍና በደል ሲፈፀም አይቶ እንዳላየ መሆን ሲልም ይህን ከሚፈፅሙ አምባ ገነኖች ጎን ለሚጣልላቸዉ ሳንቲም ሲሉ መቆም አሳፋሪዉ የዛሬ ምሑራን መገለጫ ነዉ ባይ ነኝ፡፡ ስለሆነም ይህ አካሄዳቸዉ ለራሳቸዉም ሆነ ተቸግሮ ላስተማራቸዉ ደሀ ህዝባቸዉ የማይበጅ መሆኑን በመገንዘብ ፤ ምሑርነት የምረቃ ልብስ ለብሶ ፎቶ ከመነሳትና የድግሪ ፣ የማስትሬት ፣ የዶክትሬት ወረቀቶችን ከመሰብሰብ ባለፈ የሚመዘነዉ በሀገራዊና ህዝባዊ ጠቀሜታው መሆኑን በመረዳት የሀገራችን ምሑራን ለወቅቱ የዲሞክራሲና የፍትህ ጥያቄ መመለስ ግንባር ቀደም ተዋናኝ መሆን ይገባቸዋል እላለሁ፡፡


ድርጅትዎን በፍኖተሕብረት ሬድዮ ያስተዋውቁ !

አድራሻ 5309 Georgia Ave. Nw , Washington DC 20011

ስ/ቁጥር 202 291 4217 e-mail: dc.region.eprp@gmail.com


## ባስኪን ሮቢንስ እና ዳንኪን ዶናት


ደንበኞችን ማስተናገድ የሚችሉ ሠራተኞችን መቅጠር ይፈልጋል።

ይሥራ ሰዓት ከ4 ሰዓት እስከ 5 ሰዓት ማልዶ መገባት የሚችል።

አድራሻ 2420 ኒውዮርክ አቬኑ ኖርዝ ኢስት ዋሽንግተን ዲሲ 20002

ስልክ (202) 526 3677

# ኢሕአፓ 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን በተሳካ ሁናቴ አጠናቀቀ

ቀን ነሐሴ 26 ቀን 2004 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ከነሐሴ 23 እስከ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. ከተለያዩ አህጉራት የተወከሉ የፓርቲው አባላትና አካላት በተገኙበት አካሂዷል። ጉባዔው የኢትዮጵያን ወቅታዊ የፖለቲካ፤ የማህበራዊ፤ የኤኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም ድርጅታዊ ነክ ጉዳዮችን በስፋትና በጥልቀት ከተወያየ በኋላ የተለያዩ ውሳኔዎችንና በማሳለፍና መመሪያዎችን በመስጠት በተጨማሪም ለሚቀጥሉት የሥራ ዘመን የሚያገለግሉ የአመራር አባላትን በመምረጥ በተሳካ ሁኔታ አጠናቋል።

ይህ የኢሕአፓ 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የተካሄደው ሀገራችን ኢትዮጵያ ሕልውናዋ ጭምር በአምባገነኑ የወያኔ ዘረኛና ጎሰኛ ቡድን ከምንጊዜውም በበለጠ አደጋ ላይ በወደቀበት ፤ ፖለቲካዊ፡ ኤኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ ቀውሶቹ ተባብሰው ይህ ነው የማይባል ደረጃ ላይ በደረሱበት፤ አገዛዙ ከውስጥና ከውጭ አድሃሪ ኃይሎች ጋር በመተባበር የሕዝባችንን የዴሞክራሲና የሙብት ጥያቄዎች ደብዛ ለማጥፋት በሚሯሯጥበትና መጠነ ሰፊ የሆነ የፕሮፖጋናዳ ውዥንብር እየነዛ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱ የሚደርሱበትን ጥቃቶች ተቋቁሞ የውስጥ ችግሮቹንም አስወግዶ የዕለት ተዕለት ተግባሩን በተረጋጋ ሁናቴ እያከናወነ ባለበት ሁናቴ ነው። ጉባዔው የተካሄደው ፓርቲው የተመሰረተበትን 40ኛ አመት ለማክበር በመዘጋጀት ላይ መሆኑ ጉባኤውን ታሪካዊነትን አላብሶታል።

ኢሕአፓ በወያኔም ሆነ የሱ አምሳያ በሆኑ ፀረ ሕዝብና ፀረ አንድነት ኃይሎች የሚደርስበትን ጥቃት እየተከላከለ፤ ብሔራዊና ዴሞክራሲያዊ ትግሉን በአይበገሬነትና በፅናት በማካሄድ ፍፁም መግባባትና የሃሳብ አንድነትን ባንጸባረቀ፡ ጥንትም፤ አሁንም፤ ወደፊትም የማንነቱ መገለጫ የሆነውን ኢሕአፓዊነትን ባሳየ መልኩ የተካሄደና ከምንጊዜውም በበለጠ ተጠናክሮና ራሱን በአዲስ የትግል መንፈስ አድሶ የወጣበት ጉባዔ ነበር።

ጉባዔው የሥራ ዘመኑን በጨረሰው አመራር አካል የቀረበለትን የሥራ ዘገባና የተከናወኑ ተግባራትን፤ ያጋጠሙ ችግሮችን እንዲሁም የታዩ ድክመቶችን በሁለገብ መልኩ የዳሰሰውን ሪፖርት የመረመረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች እየታዩ ያሉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በርካታውን ሕዝብ ለሕዝባዊ አመፅ የሚገፋፋ ሁኔታ መኖሩን ተገዝቦ ይህን ትግል ለማፋፋም አመቺ የሚሆኑ የተግባር ውሳኔዎችንም ያሳለፈበትና የወደፊት እቅዶቹንም የነደፈበት ነበር።

ከሁሉም በላይ ኢሕአፓ ላለፉት በርካታ አመታት ሕዝባዊ ትግሉ ፈሩን እንዳይለቅ ያደረጋቸው አቅጣጫ የማስያዝ ቅስቀሳና የማደራጀት ተግባሮቹ መልክ የያዙበት በመሆኑ፤ እንዲሁም በወያኔ አገዛዝና በሕዝቡ መካከል ያለውን የማይታረቅ መሰረታዊ ቅራኔ ለማስወገድና የወያኔን አገዛዝ መጣል ይቻል ዘንድ ለሀገር አንድነትና ለዴሞክራሲ ከቆሙ ኃይሎች ጋር ለመተባበር ያደረገውን ጥሪ በዚህም ጉባዔ በማጠናከር በአዲስ ለተመረጠው የድርጅቱ አመራር ይህንን ውሳኔ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችልበትን እቅድ አውጥቶ እንዲንቀሳቀስ መመሪያ ሰጥቶታል።

በመጨረሻም ጉባኤው በተወያየባቸው ጉዳዮች ላይ ጠቅላላ ውሳኔዎችን አፅድቆና ስሜት ቀሳቃሽና የማንነቱ መግለጫ የሆነውን „የትግሉ ነው ሕይወቴ" የተባለውን መዝሙር በደመቀ ሁኔታ በመዘመር በጥሩ ሁኔታ ተጠናቋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!**
**በትግላችን እናቸንፋለን!!**
**ኢሕ አፓ ይለምልም!!**

# የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት የአውሮፓ ክፍል ተመሰረተ

የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት የአውሮፓ ክፍል ነሐሴ 11 እስከ 13 ቀን 2004 ዓ.ም. ፍራንክፈርት ጀርመን ውስጥ በተካሄደ ጉባኤ ተመስርቷል። በዚህ መስራች ጉባኤ ላይ በርካታ ወጣቶች የተገኙ ሲሆን በሁለገብ ጸረ ወያኔ ትግል የኢትዮጵያን ሕዝብ ከግፍ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት ቆርጠው መነሳታቸውን በከፍተኛ ስሜት አረጋግጠዋል።

ይህ የምስረታ ጉባኤ ኢሕአፓ 40ኛ የምስረታ በአሉን በሚያከብርበት ታሪካዊ አጋጣሚ የተካሄደ ከመሆኑም በላይ የተጠናቀቀውም በተሳካ ሁኔታ ነበር። ለበለጠ መረጃ በፊልም የተደገፈውን ዘገባ በደብተራው ድህረ ገጽ (www.debteraw.com) ይመልከቱ: :





# ዘመናትን ያቆራረጠ የጽኑአን መዝሙር " የትግሉ ነዉ ሕይወቴ"

ብዙዎች በደረቅ ለሊት ወደሞታቸዉ ሲሔዱ ዘምረዉታል ። ትግሉ ሲከርር ፤ሲመርርም ፤ መዝለቅ ያልቻሉ የትናንት ታጋዮች ሲንሸራተቱ ፤ የትግሉ ሰማዕት በፋሽስቶችና በጎሰኞች እጅ ሲወድቁና ሲሰዉ ፤ ቀሪዎቹና ሕያዋኑ ጽኑአን ፤ ትግሉንና አብዮቱን ከዳር ለማድረስ ትከሻ ለትከሻ ቆመዉ በሲቃና በወኔ አዚመዉታል ። "የትግሉ ነዉ ሕይወቴ " በዜማና በቃላት ዉህደት ከአንደበት የሚፈልቅ የትግል ብሥራት ፤ የመስዋዕት ቃል ኪዳን ነዉ ።

በመዝሙሩ የተስተጋባዉ የተደራጀ ሕዝብ ትግል ጅማሬ ብሥራት ዛሬም አልደበዘዘም ። ቃል ኪዳኑም ከቶ አልታጠፈም። የትግሉን ፋና በወጋዉ ቀዳሚ ትዉልድና በተከታዮቹ ትዉልዶች መሃከል ኢትዮጵያ ዉስጥ ሕዝባዊ ሥርዓት እስኪተከል ድረስ ለሚደረግ ትግል ቀጣይነት የጋራ ራዕይ ማስተሳሰሪያ ሃብል ሆኖ ዘልቋል ። በዚህም ሳቢያ ዕድሜኔና ትዉልድን ባቃየጡ የፖለቲካ መድረኮች ላይ ሁሉ ወጣቶች ፤ጎልማሶችና አረጋዉያን የተዘረጉ እጆቻቸዉን እያይዘዉ በመቆም ሲያዜሙት መመልከት የተለመደ ነዉ ።

በይዘቱ ፤ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን "ከጭቆና ማጥ" ለማዉጣትና ፍትህ ፤እኩልነትና ዴሞክራሲ የሰፈነበትን ሥርዓት ለመመስረት ራዕይ የነበረዉን ትዉልድ ቁርጠኛነት በአንክሮ ያስተጋባል:: ያ ትዉልድና ዓርማዉን አንግቦ የሚታገለዉ ተተኪ ትዉልድ ፤ራዕዩን ዕዉን ለማድረግ በይፋ ለመታገል አልታደለም ። በስሩ ተሰልፎ የሚታገልበት ፓርቲ -ኢሕአፓ ህቡዕ ድርጅት ነበር፤ ዛሬም ነዉ ። የኢሕአፓና የኢሕአፓነት መገለጫ ተደርገዉ የሚወሰዱት ሌሎች ነገሮችም እንደዚያዉ ህቡዕ ናቸዉ። በቀትር ጸሃይ አደባባይ ከመታዬት የኢህጋዉያኑ ገዢዎች "ህግ" ያገዳቸዉ ነበሩ ። የኢሕአፓ ዓርማ ፤ የድርጅቱ ልሳን (ዴሞክራስያ )እና በዘልማድ የኢሕአፓ "የሕዝብ መዝሙር" ተብሎ የሚታወቀዉ "የትግሉ ነዉ ሕይወቴ" ለአብነት የሚጠቀሱ መገለጫዎች ናቸዉ ። ከነዚህ ጋር የተጠረጠረ ንክኪ ደግሞ ለሞት ፤ ለስቃይና ለእስራት የሚዳርግ "ወንጀል" ሆኖ ከህግ ዉጭ ተደንግጓል ።

በሀገራችን ታሪክ ዉስጥ፤ ለፍትህ፤ ለዴሞክራሲና ለእኩልነት ትግል ከተጀመረባቸዉ ከ፲፱፻፷ዎቹ ዓመታት ወዲህ ሦስት፤ " ብሔራዊ "መዝሙሮች ተፈራርቀዋል ። በስያሜ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተብለዉ ይታወቁ እንጂ መዝሙሮቹ ግና እያንዳንዳቸዉ የተቀመሩበት መሠረተ ሃሳብ ከሕዝቡ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ አልነበረዉም ። የንጉሡ ዘመን መዝሙር ፤ ኢትዮጵያ በንጉስዋ ደስ ብሏት ለዘለዓለም እንድትኖር ፤ለሕዝቧም ክብር ንጉሡን እንዲያኖራቸዉ የሚማጸን ነበር ። ከሥርዓቱ ጋር ቀርቷል ።በመቀጠል ፤ ወታደራዊ ደርግ በበኩሉ እንዳቅምቲ " ኢትዮጵያ ትቅደም'' ፍልስምናዉ መሆኑን እያንባረቀ ተተካ ። በአቶ አሰፋ ገብረማሪያም ተሰማ ገጣሚነት፤ ደርግ ይልበሰዉም ያሸርጠዉም "ኢትዮጵያ ቅደሚ " የሚል ጥብቆ ተሰናዳለት ። የደርጉ ሊ/መንበር -በኋላም ፕሬዚዳንት የነበረዉ ኮሎኔል መሠረትኩት ያለዉን "ሪፑብሊክ" በትኖ ሲፈረጥጥ ፤ መዝሙሩም ለአንድ ሰሞን ከተተኪዎቹ ጎሰኞች ጋር አዲስ አበባ ስታዲየም ዉስጥ እንካ ስላንትያ መግጠሚያ ሆኖ ከረመና ለፍጻሜዉ ተሰናበተ ።ደርግን ደግሞ ባለተራዎቹ ጎሰኞች-ወያኔዎች በሊ/መንበራቸዉ ተኩት

። አቶ ደረጀ መላኩ ግጥሙን ፤ ሰለሞን ሉሉ ደግሞ ሙዚቃዊ ድርሰቱን አበረከቱና ጎሰኛዉ አገዛዝ " ታዬ ሕዝባዊነት" በሚሉ ሙከሻዎች ሲሽሞነሞን ሃያ አንድ ግንቦቶች ጠብተዉ አለፉ ። የወያኔዉ መሪ ሞቶ ሰኔ ላይ ግብአተመሬቱ ተፈጽሟል። አገዛዝ ፤ ቁንጮዉና መዝሙሩ አብረዉ ማክተማቸዉን ስናየዉ ኖረናልና ፍጻሜዉ የተለየ እንደማይሆን እንገምታለን።

# ትላንትና

ከሕዝብ (ብሔራዊ) መዝሙሮች ወጣ ብለን የተቀኙትን መዝሙሮችም ብንመለከት የምናገኘዉ ስዕል ተመሳሳይ ነዉ ። የአጼዉ አገዛዝ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙሮች ነበሩት። በጧትና ማታ ከሰንደቅ ጫፍ ለሚዉለበለበዉና ለሚወርደዉ ዓርማ ክብር "ደሙን ያፈሰሰ" እና "ተጣማጅ አርበኛ" በሚሉ ርዕሶች የተቀናበሩ መዝሙሮች ይዘመሩ ነበር ። የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከተገረሰሰበት ጊዜ ወዲህ ተሰምተዉ አያዉቁም ። በደርግ የአገዛዝ ዘመን ለሰንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓት ማድመቅያ መዝሙሮች ተዘጋጅተዉላቸዉ እንደነበረ ገጣሚያቸዉ የሆኑት ሰዉ ( አቶ አሰፋ ገ/ ማሪያም ) ግጥሞቹን ደብለዉ ባሰፈሩበት ህትመት ገልጠዉልናል ። ይሁን እንጂ በዘመነ ደርግ የትኛዉም የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ከሥራ ላይ አልዋለም ። ለጣቂዉ የወያኔ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከጅምሩ አንስቶ የነበረዉን የንቀት ግምት መላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያዉቀዉ ጉዳይ ነዉ ። ለክብርዋ መግለጫ የሚያገለግሉ መዝሙሮች እንዲኖሩትም የጠበቀ አንድም ኢትዮጵያዊ አልነበረም ። ወያኔም አልነበረዉም።

ወደ 7 ኛው ገጽ ዞሯል

# የትዉልድ ቅብብሎሽ፤ ከኢሕአወሊ እስከ ኢወክንድ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ከዘመናዊ ትምህርት መጀመርና መስፋፋት ጋር ተያይዞ የተማረዉና በመማር ላይ የነበረዉ ወጣት ትዉልድ በኅብረተሰቡ ዉስጥ ማበርከት የሚገባዉን ልዩ ድርሻ ቀስ በቀስ እየተገነዘበ ሄዷል ። በትምህርት ሰበብ ባህር ማዶ ለመሻገር ዕድል ያገኙቱ ወጣቶች በየሄዱባቸዉ አገሮች ሲካሄዱ የነበሩትን ማሕበራዊ አብዮቶች በቅርብ ሆነዉ ማስተዋል ችለዋል ።ይህን መሰሉን ተመክሮአቸዉንም ከአገር ቤቱ እዉነታ ጋር በማንጸር ፋይዳዉንና አንድምታዉን ማጤናቸዉ አልቀረም ።

በአገር ዉስጥ በተለይም በዋና ዋናዎቹ ከተሞች የተመሠረቱት የትምህርት ተቋማትም የወጣቱን አዕምሮ በማነጽና አዳዲስ አስተሳሰቦችን በማስረጽ የነበራቸዉ አበርክቶ ጉልህ ነበር ። ከዚህ ዉጭ ፤ እነዚሁ ተቋማት በዕድሜና በአስተሳሰብ ደረጃ መሳ ለመሳ ለሆኑ ፤ነገር ግን ከተለያየ ማኅበራዊ ዳራና የኑሮ እርከን ለፈለቁ ታዳጊ ዜጎች የወል መናኸሪያ በመሆን አገልግለዋል ።ይህም በበኩሉ በተማሪዎች መሃከል የአብሮኝነት ስሜት እንዲፈጠር፤ ዘግይቶም በትምህርት ተቋም ደረጃ በአንድነት ቆሞ ድምጽን የማሰማት ባህል ስር እንዲሰድ አስችሏል።

በኢትዮጵያዉያን የዘመን አቆጣጠር በ፲፱፻፵ዎቹ ዓመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ተጸንሶ የተወለደዉና ከጊዜ በኋላ ወደ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተዛመተዉ የተማሪዎች ንቅናቄ የኢትዮጵያ ወጣቶች በየፈርጁ ያደረጉትን ትግል ማመላከቻ ነዉ ። አጀማመሩ ላይ ከፖለቲካዊ ጥያቄዎች የተፋታ ፤ ግቡም በቅጽር ግቢዉ ዉስጥ ለተከለሉ የተማሪዉ ችግሮች መፍትሔ ከማስገኘት ያላለፈ ነበረ ።ተማሪ አቀፍ ድርጅታዊ አቅምንና ፖለቲካዊ ብስለትን የሚቀዳጀዉ የራሱን የዕድገት ሂደት ተከትሎና ዘግይቶ ነዉ ።

በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም በጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ መሪነት ከተካሄደዉ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በኋላ የተማሪዎች ጥያቄ በይዘቱ ፖለቲካዊነትን፤ በቅርጹ ሀገራዊነትን እየተላበሰ ሄዷል ። ምንም እንኳ መፈንቅለ መንግሥቱ ከከሸፈ በኋላ የንጉሰ ነገሥቱን ምህረት ለማግኘት የቡድን ተማጽኗቸዉን ያቀረቡ ቢሆንም የመንግሥት ግልበጣዉ በተጀመረ በሁለተኛዉ ቀን በአዲስ አበባ ከተማ ይገኙ ከነበሩት ኮሌጆች የተዉጣጣ የተማሪዉ ልዑክ ወደ ክብር ዘበኛ ጦር ጠቅላይ መምሪያ በመሄድ በጀኔራል መንግሥቱ የተደረገለትን ገለጻ አዳምጧል

በነገታዉም በከተማዉ አዉራ መንገዶች ተሰልፈዉ በመዉጣት ታሪካዊዉንና ዝነኛዉን የ"አትነሳም ወይ" መዝሙር እያዜሙ ለለዉጡ ያላቸዉን ድጋፍ በይፋ ገልጸዋል ። ይህ አጋጣሚ የተማረዉ ወጣት የኅብረተሰብ ክፍል እንቅስቃሴ ዉሎ አድሮ የሚከተለዉን የስር ነቀል አብዮት አቅጣጫ ጠቋሚ ነበር ። እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ዉስጥ በፖለቲካዉ መድረክ ላይ ከሚንከላወሱት ግዙፋን ጉዳዮች፡- የመሬት ባለቤትነትን ጥያቄ ፤ የብሔርን ጥያቄ ፤ ከኃያላኑ መንግሥታት ተጽዕኖ ሥር ያልወደቀ ብሔራዊ መንግሥትን ጥያቄ፤ ...ወዘተ የመሳሰሉቱ የመታገያ መፈክሮች ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀመሩትም ሆነ የተስተጋቡት በወቅቱ በነበረዉ የተማረ ወጣት ትዉልድ አማካይነት ነዉ ። የዚያኑ ያህል በወቅቱ በኅብረተሰቡ ዉስጥ ሲካሄድ በነበረዉ የመደብ ፍትጊያ ዉስጥ ጎራ ለይቶ ከተጨቋኞቹ ጋር በመቆም ምዝበራን የመቃወምና የመታገልን ፋና የወጋዉም ይኼዉ ወገን ነዉ።

በተማሪዎች ማሕበራት አማካይነት ሲደረጉ በነበሩት የትግል እንቅስቃሴዎች ዉስጥ በመሳተፍ ወጣቱ የተማረ ትዉልድ ራሱን ለላቀ ፖለቲካዊ ግብና ሀገራዊ አድማስ ለሚያካልል አዲስ አብዮታዊ ተልዕኮ እያዘጋጀ ነበር ። ወጣቱን ትዉልድ ለሥር ነቀል የማኅበራዊ ሥርዓት ለዉጥ ለሚደረግ ትግል መስመር አስይዞ የማሰለፉ ተግባርና ሀላፊነት ደግሞ የተማሪዉን ንቅናቄ ከሚያቀናብሩት ማህበራት አቅም በላይ የሆነ ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነበር ። ችግሩን በወቅቱ የተገነዘቡ ጥቂት ታጋይ ተማሪዎች ከተለመደዉ የተማሪዎች ድርጅታዊ ቅርጽ በመዉጣት መሰል ወጣቶችን ያሰባሰቡ የጥናት ክበቦችን ከት/ቤት ቅጽር ግቢ ዉጭ ማደራጀት ጀምረዉ ነበር ።በጥናት ክበባት ዙሪያ የመሰባሰቡ ሁኔታ እስከ ጠቅላይ ግዛት ከተሞች ድረስ ዘልቆም ነበር ።

ይኼዉ ድርጅታዊ ጥያቄ ፤የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በኢትዮጵያዉያን የዘመን አቆጣጠር በሚያዝያ ፲፱፻፷፬ ዓ.ም እስኪመሠረት ድረስ መልስ ሳያገኝ ቆይቷል ። ኢሕአፓ ፤ ሙሉ በሙሉ ወጣት-ነክ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ራሱን ያስጠመደ ድርጅታዊ ክንፍ ሊኖረዉ እንደሚገባ ገና ከጅምሩ አስቦበታል ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ነጻ ሀሳብ

## <<እየሞተ>> ያለዉ የምሁራን የፖለቲካ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ፤ ድሮና ዘንድሮ

ክበያ

ብዙ ግዜ "የዛሬን አያድርገዉና" ይላሉ አባቶቻችን ትረካቸዉን ሲጀምሩ - የትናንቱን ዛሬ ላይ አለመኖር በቁጭት ለመጥቀስ ያህል:: እኔም የትናንቱን ሞቅ ደመቅ ያለ የምሁራን የፖለቲካ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ከዛሬዉ ሁኔታ ጋር ሳስተያየዉ እንደነሱ የዛሬን አያድርገዉና ብሎ በቁጭት መጀመሩን ወደድኩ ::

የዛሬን አያድርገዉና ድሮ ድሮ በተለያየ ሀገራዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ በቀጥታ መሳተፍ እንዲሁም በወቅቱ ጎልተዉ ይሰሙ በነበሩ የተለያዩ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች ላይ መወያየትና መከራከር የምሁራን መገለጫ ነበር:: ያዉም ትልቁና የሚያኮራ መገለጫ:: በቃ! ምሁር ማለት ለሀገሩ የፖለቲካ ችግር መፍትሔ የሚያፈላልግ ፤ ለለዉጥ ከወገኖቹ ፊት ቀድሞ የሚቆም የለዉጥ አርበኛ ነበር ቢባል ይቀላል::

እዚህ ላይ ምሁር ስል የዩኒቨርስቲ ተማሪወችን ይጨምራል:: በወቅቱ የቀድሞዉ የአፄ ሀይለስላሴ ኮሌጅ የዛሬዉ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የዚህ እንቅስቃስቃሴ መናገሻ ሲሆን በግቢዉ ዉስጥ ፖለቲካ <<ይወለድ>> ፣ ይሰበክ ፣ <<ይሰበቅ>> ነበር - የዛሬን አያድርገዉና:: እንቅስቃሴዉ ጠንከራ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በግቢዉ ዉስጥ የተለያዩ የፓለቲካ አጀንዳ ያነገቡ መፅሔቶች ፣ ጋዜጣወችና በራሪ ወረቀቶች ይታተሙና ይሰራጩ ነበር::

ከዚህም ባሻገር ትልልቅ የዉይይት ፕሮግራሞች ይዘጋጁና የሃገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ይዳሰስና ይተነተን ነበር:: እንደ አስፈላጊነቱም የተቃዉሞ ሰልፎች ይካሄዱ ነበር:: ይህ ዘመናዊ ሊባል የሚችል ምሁራንን በግንባር ቀደምነት ያሳተፈ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ ላይ ተከታትለዉ ለታዩት የፖለቲካ ለዉጦች ትልቅ መሰረት ሆኖ ያለፈ ሲሆን እንደ ትልቅ የታሪክ ክስተትም ሁሌ ሲታወስ ይኖራል::

በንጉሱ ዘመን የሀገራችን ምሁራን በወቅቱ የነበረዉን በዝባዝ የጭሰኛ ስርአት ፣ የሰብዓዊ መብት ረገጣና የመልካም አስተዳደር ችግር ያወገዙና የታገሉ ሲሆን በመጨረሻም የ66ቱን አቢዮት በማነሳሳትና በማቀጣጠል የአገዛዙን ቁንጮ ከሰማይ ተሰጠኝ ከሚሉት ስልጣናቸዉ አዉርደዉ ስርዓቱን ዳግም ላይነሳ ገርስሰዋል:: ይህ አቢዮት ምንም እንኳን በመጨረሻ ሰዓት ላይ ሳይታሰብ ስልጣኑን በጨበጠዉ ወታደራዊዉ ደርግ የተነሳ ግቡን ሙሉ ለሙሉ ባይመታም ህዝቡን እንደ መዥገር ተጣብቀው ለፍቶ ማስኖ የሚያገኘዉን እየነጠቁ ግፍ ከሚፈፅሙበት የወቅቱ ባላባቶች ነፃ አዉጥተዉታል::

ይህ የፖለቲካ እንቅስቃሴና አቢዮት ከሀገራዊ ጠቀሜታው ባለፈ ለመላዉ ጭቁን የጥቁር ህዝብ ከነጭ አምባገነናዊ የኢምፔሪያሊት ስርዓት ነፃ የመዉጣት ተስፋን የፈነጠቀ መልካም ተመክሮ መሆን ችሏል:: ይህ የምሁራን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከንጉሱ መዉደቅ ከስርዓቱ መፈራረስ በኃላም የቀጠለ ሲሆን፡ በድህነት አረንቋ ተዘፍቆ የቆረቆዘዉን ፣ በመልካም አስተዳደር እጦት የሚሰቃየዉን ፣ ሰብአዊ መብቱ የተገፈፈዉን ህዝባቸዉን ብሶት በማዳመጥ ሳይታሰብ ስልጣን የጨበጠዉን አምባገነን የደርግ መንግስት በፅኑ ተቃዉመዋል::

የህዝቡ ጥያቄ እንዲመለስ በድፍረትና በወኔ ታግለዋል:: ምንም እንኳን አገዛዙ የለየለት ጨካኝና አረመኔ በመሆኑ ምላሹ ጥይት የነበረ ቢሆንም እነዚህን ለነፃነትና ዲሞክራሲ የቆሙ ምሁራንን ግን ፍፁም መግታት አልቻለም ::

በአጠቃላይ እነዚህ በወቅቱ የነበሩ ምሁራን ምንም እንኳን ሹልክ እያሉና እንደ ቀበሮዉ ባህታዊ የደግነት ለምድ ለብሰዉ በማጭበርበር ስልጣን በጨበጡ አንባገነኖች ጥያቄያቸዉ ሙሉ በሙሉ ባይመለስም በወቅቱ የህዝቡን ጥያቄ በሰፊዉ አስተጋብተዋል ፤ እንዲመለስም በፅኑ ታግለዋል:: የቀሰሙትን እዉቀት በመጠቀም ከመንጋጋዉ ፈልቅቆ ላስተማራቸዉ ህዝብ ዉለታቸዉን ከፍለዋል:: ታሪክ ቀይረዋል ፤ ታሪክ በደምና በላባቸዉ ፅፈዋል:: የመማርን ትርጉም በተግባር አሳይተዋል:: ከዚህ ህዝባዊ ስራቸዉ ጋር በተያያዘ ምናልባት ምሁራት የመላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ወኪል ነበሩ ቢባል ማጋነን የሚሆን አይመስለኝም::

ይሁንና ዛሬ ዛሬ ይህ በምሁራን መካከል ይደረግ የነበረ ሞቅ ደመቅ ያለ የፖለቲካ እንቅስቃሴና ተሳትፎ በሚያሳዝን ሁኔታ እየተረሳ የመጣ የብዙወቻችንን አንጀት የበላ ጉዳይ ሆኗል:: ምንም እንኳን ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬም በድህነት፣ በረሃብ፣ በበሽታ፣ በመልካም አስተዳደር እጦት፣ በፍትህ መዛባት፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ በሙስና...እየተናጠች ብትገኝም በምሁራን ቤት ዉስጥ የዝምታ ፋሽን አይሉት በሽታ ነግሷል:: በሀገራዊ የፖለቲካ ሁኔታዎች ላይ መወያየትና መከራከር የምሁራን መገለጫነቱ ያበቃለት መስሏል:: ፖለቲካዊ <<ዝም ጭጭ>> የምሁራን ዋነኛ መታወቂያ ሆኗል::

ምንም እንኳን ከቅርብ ግዜ ወዲህ ዩንቨርስቲዎችና መሰል ትላልቅ የትምህርት ተቋማት እንደ አሸን እየፈሉ ቢሆንም ፤ በመቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በየአመቱ በዲፕሎማ ፣ በድግሪ ፣ በሁለተኛ ድግሪ ፣ በዶክትሬትና በመሳሰሉት የትምህርት ደረጃዎች ቢመረቁም በተቃራኒዉ የህዝብን ብሶት አዳምጦ መፍትሄ የሚያፈላልግ ምሁር ግን የህልም እንጀራ እንደሆነ ነዉ:: ለምን ድህነት ፣ ረሃብ፣ በሽታ ፣ የመልካም አስተዳደር እጦት ፣ የፍትህ መዛባት ፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ሙስና... ብሎ የሚመክር ፣ የሚጠይቅና የሚታገል ምሁር የትናንቱ ታሪካችን ብቻ ሆኖ ቀርቷል::

ይልቁንም በሀብት የተትረፈረፉትና የተንደላቀቀ ህይወት የሚመሩት ምዕራባዉያን እንደ ግዜ ማሳለፊያ የሚጠቀሙበት የመዝናኛ ኢንዱስትሪያቸዉ ለዛሬ ምሁራን የተሻሉ የዉይይትና የክርክር አጀንዳወች ሆነዋል ማለት ይቻላል ፤ ወጣት ምሁራን የነዚህን የመዝናኛ ኢንዱስትሪወች ትዕይንት ሲተነትኑና በነሱም ላይ ሲፈላሰፉ ዉሎ ማደርን መርጠዋል ::

እንደሚታወቀዉ በወቅቱ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ብዙ የመወያያ ፣ የመመካከሪያ... አማራጮችን ፈጥሯል ፤ ነገር ግን ለኛ ምሁራን የሙዚቃ ማዳመጫ ፣ የፊልም መመልከቻ እንዲሁም የፎቶግራፍ መለጠፊያ ከመሆን በዘለለ ለተሻለ ተግባር ሲያገለግሉ አይስተዋልም:: እዚህ ላይ እስቲ አንዴ ቆም ብለን እንጠይቅ ፤ ስንቱ ምሁራን ናቸዉ ማህበራዊ ድህረ ገጾችን ለወገናቸዉ ለሚበጅ ተግባርና ቁም ነገር የሚጠቀሙበት ? ፤ ማለቂያ የሌለዉ ሰላምታ ከማዥጎድጎድና የመልካም ልደት መልዕክቶችን ከመለዋወጥ በዘለለ ስንቶች ናቸዉ ስለሀገራችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኪሳራ የተወያዩበት? ዛሬ ከምዕራባዉያን አልፎ ጎረቤቶቻችን እንኳን የነዚህን የፈጠራ ውጤቶች ጠቀሜታ ተረድተው የማህበራዊ ፣ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ መሻሻል ለማምጣት እየተጠቀሙባቸዉ ባሉበት ሰዓት የኛ ምሁራን መቀለድን መምረጥ ለኔ ግራ የሚያጋባና የሚያናድድ ጉዳይ ሆኗል::

አንዳንድ ሰዎች ከዚህ የፖለቲካ <<ዝምጭጭ>> ጋር በተያያዘ የወቅቱ አምባገነኖች ዛቻና ማስፈራሪያ እንዲሁም በነፃነት ለመናገርና ለመቃወም የማያስናዝሩ ህጎቻቸዉ ምክንያት ናቸዉ ይላሉ፤ ምሁራት በሚያስተምሩባቸዉና በሚማሩባቸዉ ዩኒቨርስቲዎች ፣ ኮሌጆቻች እና መሰል የትምህርት ተቋማት እንዲሁም በሚሰሩባቸዉ የመንግስት ተቋማት ዉስጥ አፋኝ ተፅዕኖ ተደርጎባቸዉ ነዉ ሲሉ ይደመጣል:: ግን እዚህ ላይ ጥያቄዬ ምሁር በነዚህ ተፅዕኖ እጅ ይሰጣል ወይ ነዉ:: እንደኔ አይሰጥም ባይ ነኝ:: እነዚያ የትናንት ወጣት ምሁራን ያን ማድረግ የቻሉት ዛቻና ማስፈራሪያ እንዲሁም አፋኝ ተፅዕኖ ስላልነበረባቸዉ ይሆን ? አይደለም! ይልቁንም ከዛቻና ማስፈራሪያዉ በላይ የህዝባቸዉ ስቃይና መከራ ተሰምቷቸዉ ነዉ ፤ የተሸከሙትን ህዝባዊ ሀላፊነት በደንብ ተረድተዉት ነዉ ፤ ከህሊና ፀፀት ለመዳን ነዉ ፤ የመማራቸዉ የመመረመራቸዉ መገለጫ በድህነት ፣ በመልካም አስተዳደር እጦት፣ በፍትህ መዛባት፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰት... የሚማቅቀዉን ህዝባቸዉን መታደግ መሆኑን ተገንዝበዉ ነዉ ባይ ነኝ:: ምናልባትም ዝምጭጩ የ ሎሌነት መገለጫ ነዉ አሊያም ህዝባዊ ሀላፊነትን ከመዘንጋት ነዉ ቢባል ሳይሻል አይቀርም ::

እርግጥ ነዉ <<የዝምጭጩን>> ጉዳይ አስቀድሜ አነሳሁት እንጅ ከዛም ባለፈ ለጥቅማጥቅምና ስልጣን ሲሉ ተቸግሮ ያስተማራቸዉንና ከነሱ ብዙ የሚጠብቀዉን ደሀ ህዝብ ወደጎን ገፍትሮ ከአምባገነኖች ጎን መቆምና ለነሱ ክብርና ስልጣን እንዲሁም ረጅም እድሜ <<የዉዳሴ>> ቃላትን መደርደርም በምሁራን አካባቢ እየተለመደ መጥቷል:: በርግጥም በማህበረሰባችን ላይ ጭቆናን የጫነዉ አገዛዝ ተማረ በሚባለዉ የህብረተሰብ ክፍል የተገነባና የተደገፈ ነዉ :: እናም ባጠቃላይ የዛሬወቹን ምሁራን ከትናንትነዎቹ ጋር ሳነፃፅራቸዉ ብዙ የዘነጉት ነገር እንዳለ ይታየኛል:: ከነሱ በማይጠበቅ ሁኔታ በህዝብ ላይ ግፍና በደል ሲፈፀም አይቶ እንዳላየ መሆን ሲልም ይህን ከሚፈፅሙ አምባ ገነኖች ጎን ለሚጣልላቸዉ ሳንቲም ሲሉ መቆም አሳፋሪዉ የዛሬ ምሁራን መገለጫ ነዉ ባይ ነኝ:: ስለሆነም ይህ አካሄዳቸዉ ለራሳቸዉም ሆነ ተቸግሮ ላስተማራቸዉ ደሀ ህዝባቸዉ የማይበጅ መሆኑን በመገንዘብ ፤ ምሁርነት የምረቃ ልብስ ለብሶ ፎቶ ከመነሳትና የድግሪ ፣ የማስትሬት ፣ የዶክትሬት ወረቀቶችን ከመሰብሰብ ባለፈ የሚመዘነዉ በሀገራዊና ህዝባዊ ጠቀሜታው መሆኑን በመረዳት የሀገራችን ምሁራን ለወቅቱ የዲሞክራሲና የፍትህ ጥያቄ መመለስ ግንባር ቀደም ተዋናኝ መሆን ይገባቸዋል እላለሁ::

# የትግሉ ነው ህይወቴ

ከገጽ 5 የዞረ

በአገር ደረጃ ከሚጠቀሱት ከነዚህ መዝሙሮች ዉጭ ሌሎች አልነበሩም ማለት አልነበረም ። በተለይ በደርግ አገዛዝ ዘመን ከነበረዉ የዘመቻና የእናት ሀገር ጥሪ ጋጋታ አንጻር በገፍ ነበር የሚመረቱት ። ሌላዉ ቀርቶ ደርግ በመኢሶን ካድሬዎች አዝማችነት በኢትዮጵያ ምድር ላሰፈነዉ ጽልመታዊ የ"ቀይ ሽብር" ዘመን በርካታ መዝሙሮች ተቀናብረዉለታል ። ደርግ ፤ ኢማሌድሕ ፤ ኢሠፓአኮ እና ኢሠፓ ፤ ዘለቄታዉ አላማገረላቸዉም ።እንጂማ በአገር አሉ የተባሉ ገጣሚዎች፤ የዜማ ደራስያንና የሙዚቃ አቀናባሪዎች ምርጥ መዝሙሮቻቸዉን ቸረዋቸዋል ። ድምጻ መረዋዎቹ ከያንያንም በህብር አቀንቅነዉላቸዉ ነበር።በሚሊዮኖች ብር በሚሰላ የአገር ሃብት ወጪ ዘለዓለማዊነት አልተገዛምና ሁሉም ካወደሱት አገዛዝ ጋር ሞተዉ መቃብር ተጋርተዋል ። ሁሉም የመደመጫ ጊዜያቸዉን ጨርሰዉ ዳግም ወደማይደመጡበት አልፈዋል ።

"የትግሉ ነዉ ሕይወቴ" ግን ከላይ ከተዘረዘሩት ሁሉ ይለያል ።መዝሙሩ ከተደረሰ እነሆ ፵ ዓመታት ተቆጥረዋል ። ዛሬም በመዘመር ላይ ነዉ ። ልደቱ ከትግል ጋር የተቆራኘ ነበርና ከትግሉ ርዝማኔ ዕድሜን አግኝቷል ።የመዝሙሩ ስንኞች የተጻፉትና ከዜማ ጋር የተዋሃዱት ኢትዮጵያ ዉስጥ ሳይሆን መካከለኛዉ ምስራቅ - ሶሪያ ዉስጥ በሚገኝ አንድ ወታደራዊ የማሠልጠኛ ሠፈር ፡ ጊዜዉ ደግሞ ፩፱፻፷፬ ዓ.ም ነበር ።በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ ) ጠንሳሽ ጓዶች በዚሁ ስፍራ በጦር ትምህርት ላይ ነበሩ ።የመዝሙሩ ግጥምም በዚሁ አጋጣሚ ሠልጣኝ በነበረ ጓድ አማካይነት ተደርሶ ከዜማ ጋር ተዋሃደ ።በሐርሞኒካም ታጀበ ።

በዚህ ሁኔታ ታሪከኛዉ የ፵ ዓመታት ባለጸጋ መዝሙር "የትግሉ ነዉ ሕይወቴ" በትግሉ ሜዳ ተወልዶ ፤ ተከታዩን ትግል ለመያያዝ ቀይ ባህርን አቆራረጠ ። የመዝሙሩን ስንኞች ከዚህ በታች አስፍረነዋል ።

## የትግሉ ነው ህይወቴ

ለዘመናት በጭቆና ማጥ
በግፍ ሰንሰለት ታሥሬ
ሙብቴን ላሥከብር ፤ ጨቋኙን ልሽር
ተነሥቻለሁ ዛሬ ፤ ይኸው ታጥቄአለሁ ዛሬ

ባንድ እንደሚነሳ ተበዝባዥ ሁሉ
ለማያጠራጥር ድሉ
ፍጹም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ህይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና በተሰዉት ጓዶች ፋና

የመደብ የፆታ ጭቆና የዘረኞችን ብዝበዛ
እስከማጠፋ ትግሌን ልቀጥል
በወያኔ ላልገዛ
በበታኞች ላልገዛ

ረሀብ አይፈታኝም
ችግር አይገታኝም
ከግቤም አያግደኝም

ፍጹም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ህይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና በተሰዉት ጓዶች ፋና

የህዝቡ ታማኝ አገልጋይ ነኝ
የሰርቶ አደሩ ወታደር
ብረት አነሳሁ ለትግል ተነሳሁ
ጠላት ይፍራ ይሸበር ፤ ያድርባይ ቅስሙ
ይሰበር

ቢወቀጥ አጥንቴ
ቢንቆረቆር ደሜ
ላዲስ ስርአት ልምላሜ
ፍጹም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ህይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና በተሰዉት ጓዶች ፋና

# የትዉልድ ቅብብሎሽ፤ ከኢሕአወሊ እስከ ኢወክንድ

ከገጽ 5 የዞረ

በዚህም መሠረት ፤ የወጣቱ ቅርንጫፍ ድርጅት እንዲመሠረት የፓርቲዉ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሶስተኛ ጉባዔ ዉሳኔ አሳለፈ ። ዉሳኔዉን ተከትሎም የምስረታ ሕግና የመተዳደሪያ ደንቦችን ቀረጸለት ።

በአብዛኛዉ ሕብረተሰብ ዘንዳ ፤ ኢሕአወሊ በሚል አህጽሮተ ቃል የሚታወቀዉን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ወጣቶች ሊግ የማደራጀቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በኛዉ የዘመን አቆጣጠር በ፩፱፻፷፯ ዓ.ም መገባደጃ ላይ ተጀመረ ። በወቅቱ ድርጅቱን የማዋቀር ሃላፊነት የተጣለበት አንድ ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ ተመሥርቶ ሥራ ጀምሯል ። አደራጁ ኮሚቴ ከኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጋር የሚያደርገዉን ግንኙነት የሚያካኼደዉ የኮሚቴዉ ጊዜአዊ ጸሐፊ በነበረዉ በአክሊሉ ሕሩይ አማካይነት ነበር ።

አደራጁ ኮሚቴ ያደረገዉ ጥረት ሰምሮ ቀዳሚዎቹ የወጣቱ ሊግ ህዋሳት የስድስት ኪሎና የአራት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ተጎራባች በሆኑት አካባቢዎች ሊመሠረቱ በቅተዋል ። በሊጉ የመዋቅር አዘረጋግ ረገድ ፈጣን ዕድገትን ያስገኘ ሌላ ተጨማሪ ተግባራዊ ርምጃ ዉሎ አድሮ ተወሰደ። ይህም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ከድርጅቱ ዉጭ በየፊናቸዉ ተመስርተዉ ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ ተቀራራቢ ዓላማ ከነበራቸዉ የፖለቲካ ስብስቦች ጋር ዉህደት ለማድረግ የጀመረዉ እንቅስቃሴ ነበር ። ይህም ቀደም ካለዉ የተማሪዎች እንቅስቃሴ አንስቶ በትግሉ ዉስጥ በነበራቸዉ ተሳትፎ የቅስቀሳና የማደራጀት ልምድ የቀሰሙ በርካታ ንቁ ወጣቶችን አዲስ በተፈጠረዉ ድርጅት ጥላ ሥር ተሰባስበዉ እንዲታገሉ ለማድረግ አስችሏል ።

የዘመኑ ወጣት ትዉልድ ለለዉጥ የነበረዉ ከፍተኛ ተነሳሽነትና ዝግጁነት ለሊጉ ፈጣን ዕድገት መወጣጫ ሆነ ። የኢሕአወሊ ድርጅታዊ መዋቅር በአጭር ጊዜ ዉስጥ መላዉን አገር አዳረሰ ።በ ፩፱፻፷፯ ዓ.ም የተከናወነዉ የዕድገት በሕብረት ዘመቻ የወጣቱ ድርጅታዊ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ከዚያ ቀደም ታይቶ በማያዉቅ ሁኔታ እንዲመነደግ ያስቻለ ልዩ አጋጣሚ ይዞ ብቅ አለ። በቁጥር ከሃምሳ ሺህ በላይ የሆኑ የዩኒቨርስቲና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደገጠሪቱ ኢትዮጵያ ተሰራጩ ። አጋጣሚዉን በመጠቀምም ኢሕአፓ/ኢሕአወሊ የተዘመተባቸዉን ወረዳዎች ተከትለዉ መዋቅራቸዉን ዘርግተዋል። ይህ ብቻም አይደል ፤ ሕዝባዊዉን ትግል ሕዝቡ መሃከል ሆነዉ ለመምራትና በተለያዩ መስኮች ኀብረተሰባዊ ተሞክሮአቸዉን አዳብረዋል ።

ኢሕአወሊ፤ ወጣቱ ታጋይ ከዋናዉ ድርጅት ጋር ከመቀላቀሉ በፊት ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከቱን የሚያነጥርበት ፤ በድርጅታዊ ትግል የሚበስልበት ፤ በሥነ ስርአት ታንጾ የሊጋ ዕድሜዉን ባህሪያት የሚያለዝብበት ትምህርት ቤት ብቻ አልነበረም ። ኢሕአፓ እንደ ድርጅት በኅብረተሰቡ ዉስጥ የሚታወቅበት ገጽታዉም ጭምር እንጂ ። በሰላማዊ ሰልፎች ዝግጅት ፤ በቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ የመስክ ሥራዎች ፤ ወዘተ ....ዉስጥ የኢሕአወሊ አባላት የነበራቸዉ ተግባራዊ ተሳትፎ እጅጉን የላቀ ነበር ። በሀገራችን የረዥም ዘመናት እድሜ ፤ወጣቱ ትዉልድ በወርቅ የተጻፈ ደማቁን ታሪክ ያስመዝገበበት ጊዜ ቢኖር በኢሕአፓ/ኢሕአወሊ የድርጅትና የትግል ዘመን መሆኑ በፍጹም አከራካሪ አይሆንም ።

በዚሁ ትግል ዉስጥ ላደረገዉ ንቁ ተሳትፎ ምላሽ ለተከፈተበት መንግሥታዊ ሽብርና ፍጅት ሰለባ ሆኖም የህይወትና የአካላዊ ስቃይ ዋጋ ከፍሎበታል ።ታስሯል ፤ ተገርፏል ፤በስዉርና በአደባባይ ተገድሎም ሬሳዉ እንዳልባሌ ዕቃ የትም ተጥሏል ።ለኢሕአወሊና በሥሩ ተደራጅተዉ ለታገሉ ወጣቶች ሁሉ የአገር፤ የሕዝብና የድርጅት ፍቅር ምን ያህል እንደሚያስከፍል ማስተማር አይቻልም ። ኖረዉታል ፤ ግማደ መስቀሉንም በትከሻዎቻቸዉ ተሸከመዉ ክብደቱን ተፈትነዉበታል። በዚህ መሰሉ አስከፊ ሁኔታ ዉስጥ ፤ ትግሉ ባይሞትም እንኳ ድርጅታዊ ህልዉናዉ ቀድሞ በነበረዉ አኳኹዋን ሊቀጥል አለመቻሉ ግልጽ ነበር ። በ፩፱፻፸ዎቹ ዓመታት በየከተማዎቹ ተዘርግተዉ ከነበሩት የኢሕአወሊ መዋቅሮች አብዛኛዎቹ ከአገዛዙ በተሰነዘረባቸዉ አረመኔያዊ መንግሥታዊ ሽብር ተመትተዉ ነበር ። ፋሽስታዊዉ ደርግና የሽብር ግብረ አበሮቹ አያሌ ወጣት ታጋዮችን ገድለዉ በጅምላ ቀብረዋል ። ትግሉንም ጭምር መቃብር ስለማዉረዳቸዉ ግን ራሳቸዉም ቢሆኑ በፍጹም ርግጠኞች አልነበሩም።

አዎ ፤ሕዝባዊ ትግል ሊሞት አይቻለዉም ነበርና ፤ ነባሩ ለአዲስ ትዉልድ ተረኛ አስረከቦት ፤ለሌላ ገድልና ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ተከፍቷል ። ኢሕአወሊ/ ኢሕአፓ ማልዶ ያስነሳዉን የትግል ቋያ አቀጣጥሎ የሚዘልቅ ተተኪ ድርጅት ተመስርቷል ።እነሆ የኢሕአፓ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ)ተመስርቶ የትግል እንቅስቃሴዉን ከጀመረ ሰነበተ ።

የሰሜን አሜሪካዉ የኢወክንድ ቅርንጫፍ የሦስተኛ ዓመት የልደት በዓሉን ከጥቂት ሳምንታት በፊት ያከበረ ሲሆን ፪ተኛዉን ጉባዔዉን አካሄዷል ።

በቅርቡም የአዉሮፓዉ የኢወክንድ ቅርንጫፍ መሥራች ጉባዔዉን አጠናቋል ። ይህን በተመለከተ የተጠናቀረዉን ዘገባ በዜናዉ ክፍል ይመልከቱ።









## 40 ኛው እመት የኢሕአፓ ምስረታ በአል



ያስለቃሽ አልቃሾች ተጠቃሚና አድርባይ በወያኔ ኤምባሲ ውስጥ፣ ➡

በመለስ ትእዛዝ ለተጨፈጨፉት ተቆርቋሪዎች ከወያኔ ኤምባሲ ውጭ ተፋጠው ዋሉ። ⬅



